ያስከትላል። ሕጉች የገንዘብ ቅጣትና እስከ 20 ዓመት የሚደርስ የእሥራት ቅጣትን ይደነግጋሉ። ምንም እንኳን በዓመቱ ውስጥ በሰዎች የሚነግዱ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ቢውሉም፣ በተሳካ ሁኔታ ክስ የተመሠረተባቸው እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ አልታዩም።

በሰዎች በመነገድ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ለፖሊስ መኰንኖች በዓመቱ ውስጥ ሥልጠና ተሰጥቷል። የፖሊስ ተቋማት በሰዎች መነገድን በሚያካሄዱ ጥፋተኛ አሠሪዎች ላይ ክስ በሚመሠረትበት ጊዜ ለጥበቃ ወይም በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችላቸው የሀብትና የሥልጣን ውስንነት አሉባቸው።

ለፍትወተ ሥጋ እርካታ፣ በንግድና በቤት ሠራተኝነት አስገድዶ ለማሠራት አገሪቱ በተለይ ለባሕረ ሰላጤ አገሮችና ለሊባኖስ፣ በመነገጃነት ለሚላኩ ሴቶች፣ ልጆች እና አልፎ አልፎም ወንዶች ዋነኛ ምንጭ ነበረች። ከ20,000 እስከ 25,000 የሚገመቱ ሰዎች በየዓመቱ በመነገጃነት ከአገር መሄዳቸውን መያዶች ገምተዋል። በአገር ውስጥ በሰዎች መነገድም ከባድ ችግር እንደሆነ ነበር። በተለይ ለቤት አገልጋይነት፣ ለሴትኛ አዳሪነትና እንደሱቅ በደረቴ ባሉ ሥራዎች አስገድዶ ለማሠራት በአገር ውስጥ ሕጻናትና ጉልማሶች ከገጠር ወደ ከተማ ፈልሰዋል። ኢትዮጵያውያት ሴቶች በሊባኖስ በኩል ወደ አውሮፓ በመነገጃነት ሳይሻገሩ እንዳልቀረ የሚጠቁሙ ዘገባዎች ነበሩ።

ስለኤይድስና ስለሌሎች የአባለዘር በሽታዎች አደገኛነት ምንም ያልተነገራቸው ደሃ የ11 ዓመት እምቦቅቅላ ሕጻናት ሳይቀሩ በልተው ለማደር ሲሉ የሴትኛ አዳሪነት ንግድ በሚያሟጡሩ የንግድ ቤቶች መቀጠራቸውን መያዶች ዘግበዋል። ወጣት ልጃገረዶች ከአባለዘር በሽታ ነጻ ናቸው በሚል እምነት የብዙዎቹ ደንበኞቻቸው ዒላማ መሆናቸውን የ1995 ዓ.ም. የቤተሰብ ጤንነት ዓለምአቀፋዊ ሪፖርት ገልጿል።

በአንድ መያድ ዘገባ መሠረት 60% የሚሆኑት ሴትኛ አዳሪዎች ዕድሜ በ16 እና በ25 ዓመታት መካከል ነበር። ዕድሜአቸው ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ልጃገረዶች በሆቴል ሠራተኝነት፣ በመጠጥ ሻጭነትና በሴትኛ አዳሪነት በመቀጠር በመናፈሻዎችና ከባድ ተሽከርካሪዎች በሚያርፉባቸው የገጠር ከተሞች ይሠራሉ። ስር የሰደደ ድህነት፣ ከገጠር ወደከተማ መፍለስ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ኤይድስና የአባለዘር በሽታዎች፣ እንዲሁም የትምህርትና የሥራ ዕድል ውስን መሆን የልጃገረዶችን

ለሴትኛ አዳሪነት መዳረግና ቅጥ ያጣ ብዝበዛ አባብሶታል። ራሳቸውን ችለው በሴትኛ አዳሪነት ወይም በዝሙት አዳሪነት ንግድ ላይ በተሰማሩ ንግድ ቤቶች በመበዝበዝ ላይ ላሉ ሕጻናት መጠለያ በመስጠት፣ በመንከባከብና ብሎም ወደቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ በማድረግ ድጋፍ የሚያደርገውን የኢትዮጵያ የጉዳና ተዳዳሪ ሕጻናት መድረክ ጨምሮ ተጐጂ ሕጻናትን የሚረዱ ጥቂት መያዶች ነበሩ።

በሰዎች የመነገድ ተግባር "በሚያስደንግጥ መጠን እየጨመረ" መሆኑን ፍልሰት ዓለም አቀፋዊ ድርጅት (ፍዓአድ) ዘግቧል። በአገር ውስጥ የሚደረግ የሴቶችና የሕጻናት ፍልሰትን በሚመለከት በ1995 በአንድ የውጭ አገር መንግሥት የተካሄደ ጥናት ችግሩ ስር የሰደደና ሰፊ መሆኑን አመልክቷል። "የሥራ ዕድል ታገኛላችሁ በሚል አጉል ተስፋ ከገጠር ወደ አዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች መጓጓዛቸውን ብዙዎቹ የጥናቱ መላሾች አረጋግጠዋል። ጥናቱ ካካተታቸው 459 መላሾች መካከል 46% መጻፍና ማንበብ የማይችሉ ማይማን ሲሆኑ፣ 49% ደግሞ ከ8ኛ ክፍል በላይ ያልተማሩ ነበሩ። አዲሱ ሥፍራ እንደደረሱ 54% በቤት ሠራተኛነት ቢሠማሩም አብዛኛዎቹ ሴቶችና ሕጻናት በቡና ቤቶች፣ በሴትኛ አዳሪነት ወይም በልመና በመሰማራታቸው አሀዙ ወደ 9% ወርዷል።

ሕገ-ወጥ ቢሆንም፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ልጃገረዶችንና ሴቶችን ጠልፎ ትዳር መመሥረት በሰፊው ተከስቷል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)።

በግል አስተባባሪዎች አማካይነት ለቤትና ለእንዱስትሪ ሠራተኝነት ወደ ሊባኖስ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ባሕሬንና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የሚላኩ ሴቶች ቁጥር መብዛት በዓመቱ ውስጥ በማይናቅ ችግርነት ቀጥሏል። እነዚህ ሴቶች የወጡት በአብዛኛው በጂቡቲ፣ በየመንና በሶሪያ በኩል ነበር። ቤይሩት ውስጥ ከሚሠሩት 30,000 ኢትዮጵያውያት ሴቶች አብዛኛዎቹ በሰዎች በሚነግዱ የተላኩ መሆናቸውን የሊባኖስ የምርመራና የማረሚያ ማዕከል ዋና ኃላፊ ዘግቧል። በዓመቱ ውስጥ መንግሥት በውጭ አገር ለመሥራት የሚፈልጉ ሰዎችን ምዝገባ ጀምሯል። ከእነዚሁ ሴቶች 50% ያህል የሚሆኑት በሕጋዊ መንገድ ወደ አገራቸው ለመመለስ አልቻሉም።

ወደ አገራቸው ለተመለሱ በሰዎች የመነገድ ተጠቂዎች ምንም ዓይነት ከቁጥር የሚገባ የምክርና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ከመንግሥት አልተሰጣቸውም።

መንግሥት ውሱን የሆነ የቆንስላ ድጋፍ የሰጠው ለጥቂቶቹ ነው። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ለእነዚህ ተጠቂዎች የተወሰነ የሕግ ድጋፍ አድርጓል። የፌዴራል ፖሊስ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ፣ ከብዙሃን መገናኛዎች ጋር በመተባበር፣ ወደመካከለኛው ምሥራቅ መፍለስ የሚያስከትለውን አደጋ በሚመለከት የግንዛቤ ማዳበሪያ ፕሮግራሞችን ማሰራጨቱን ቀጥሏል።

በሴትኛ አዳሪነት የተሰማሩ ሕጻናትን ለመታደግ የተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕጻናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ጉዳዮች መምሪያ ሊቀመንበርነት ተመርቷል።

በሰው የመነገድ ችግርን ለመቅረፍ ከፍልሰት ዓለምአቀፋዊ ድርጅት (ፍዓድ) ጋር ምክክር በማድረግ ጭምር መንግሥት በዓመቱ ውስጥ የተወሰነ ጥረት አድርጓል። በውጭ አገር ተቀጥረው ለመሥራት ፈልገው ከአሠሪዎች ጋር ኮንትራት የሞሉ ባለጉዳዮችን የሥራ ውል ይዘት በመመርመር ረገድ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዓመቱ ውስጥ እንቅስቃሴ ያደረገ ሲሆን፣ ውሉ የማይጠቅም ሆኖ ሲገኝ አልተቀበለውም። የአውሮፕላን ማረፊያው የኢሚግሬሽን ሹማምንትም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚሄዱ ዜጐችን የሥራ ኮንትራት መርምረዋል። ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሠራተኞችን በመላክ የተሰማሩ የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ወኪሎችን የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለመቆጣጠር በመጠኑ ተሳክቶለታል። ከመንግሥት ቁጥጥርና ዕይታ ውጭ የሚሠሩ አንዳንድ ሕገ-ወጥ የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ድርጅቶች ነበሩ። ቤይሩት የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ወደዚያ የተጓዙትን ሴቶች መርዳት የቀጠለ ሲሆን፣ ተመሳሳይ ተግባር ለመፈጸም በዱባይም ሌላ የቆንስላ ጽ/ቤት ተከፍቷል።

የአካል ጉዳተኞች እኩል መብት እንዳላቸው በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፣ መንግሥት እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊውን ስልት አልዘረጋም። አንዳንድ አነስተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ዜጐች የሥራ ዕድል በማግኘት ረገድ አድልዎ እንዳተፈጸመባቸው በመግለጽ ቅሬታቸውን አሰምተዋል። መንግሥት የአካል ጉዳተኞች ወደ ሕንጻዎች መግባት የሚችሉበትን አልደነገገም፣ አገልግሎቶችን ከመንግሥት እንዲያገኙ አላደረገም። ሕገመንግሥቱ የአካልና የአእምሮ ጉዳት ለደረሰባቸወ ዜጐች መልሶ ማቋቋምና ሌሎች ድጋፎች እንደሚደረግላቸው ቢደነግግም፣ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት የመደበው ወጭ አነስተኛ ነበር።

አገር በቀል መያዶች በገለጹት መሠረት 6 ሚሊዮን ያህል የአካል ጉዳተኞች በገአሪቱ ውስጥ ነበሩ። ከኤርትራ ጋር በተደረገው ግጭት በአብዛኛው በተቀበሩ ፈንጅዎች በመጠቃት በርካታ ወታደሮች የእግርና የእጅ መቆረጥ ጉዳት ደርሶባቸዋል። የተሽከርካሪ ወንበሮች ቁጥርም አነስተኛ እና በመላ አገሪቱ በሰፊው የማይገኝ ነበር። 800,000 ያህል የአእምሮ ሕመምተኞች ቢኖሩም፣ በአገሪቱ ውስጥ አንድ የአእምሮ ሕመምተኞች መታከሚያ ሆስፒታልና 10 የአእምሮ ሐኪሞች ብቻ ነበሩ። የአካል ጉዳተኞችን በመደገፍ ተግባር ላይ የተሰማሩ 70 ያህል መያዶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ የአማራ ልማት ማኅበር በጦርነት ለተጐዱ ወታደሮች ባሕር ዳር ላይ የሙያ ሥልጠና ሰጥቷል። የትግራይ ልማት ማኅበር በበኩሉ መቀሌ ላይ ባቋቋመው ተቋሙ ሰው-ሠራሽ እጅና እግር (prostheses) በመስጠት፣ አነስተኛ የንግድ ተቋም ለሚመሠርቱ የመነሻ ገንዘብ በመስጠት፣ በማሰልጠን፣ እንዲሁም የምክር አገልግሎት በመስጠት የአካል ጉዳተኞችን ደግፏል። "ላንድማይን ሰርቫይቨርስ ኔትወርክ" የተሰኘው ዓለምአቀፋዊ መያድ በፈንጂ ለተጠቁ የአካል ጉዳተኞች የምክር አገልግሎት እና ወደ መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች መምራትን ጭምር ሰጥቷል።

## ብሔራዊ የዘር ጉዣዊ ሕዳጣን

በአገሪቱ ውስጥ ከ80 በላይ የነገድ ስብስቦች አሉ። ኦሮሞ ከሕዝቡ 40% ውን በመያዝ ብቸኛው ትልቁ ስብስብ ነው። በርካታ ክልሎች ለአገሪቱ ፖለቲካዊና ባሕላዊ ሕይወት አስተዋፅኦ ቢያደርጉም እንኳ በሰሜኑ ከፍተኛ ቦታዎች የሚኖሩት አማሮችና ትግሬዎች ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። የፌዴራሉ መንግሥት አባል ክልሎች በዋነኛ ነገዶች የአሰፋፈር ወሰን መሠረት ተካልለው፣ ክልሎች የራሳቸውን ጉዳይ በማስተዳደር ረገድ ከፍተኛ ሥልጣን ነበራቸው። አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነገድ ላይ በመመሥረት እንደተደራጁ ነበሩ።

ሠራዊቱ በነገድ ስብጥሮች እንደተደራጀ ቢሆንም፣ የከፍተኛ መኰንኖች አባላት አብዛኞቹ ከትግራይ ነገድ በመሆናቸው፣ ስብጥሩ እንደታችኛው ክፍል የተመጣጠነ አልነበረም። በዓመቱ ውስጥ ወታደሮች ኦሮሞዎችን ለመብት መጋፋት ሢላማ ስለማድረጋቸው ያልተረጋገጡ ዘገባዎች ነበሩ።

አልፎ አልፎ በቀረቡ ዘገባዎች መሠረት አስተማሪዎችና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች በክልሉ ውስጥ በነገድ ያየሉ ካልሆኑ ከሥራቸው ተፈናቅለዋል።

በአገሪቱ፣ በተለይም በምዕራብ፣ በደቡብና በምሥራቅ በኩል የጉሳዎች ግጭት እንደቀጠለ ነበር። በመንግሥትና በኦሮሞ ስብስቦች መካከል በርካታ ግጭቶች ነበሩ። በጋምቤላ፣ በደቡብ ሕዝቦች፣ እና በሱማሌ ክልሎችም ግጭቶች ተከስተዋል።

ቤንች ማጂ ዞን ውስጥ በ1995 ዓ.ም. በጉሳዎች መካከል ግጭት በተከሰተበት ወቅት አንዲት ሴትና አንድ ሕጻን ገድሏል ተብሎ በቁጥጥር ስር ውሎ የነበረው ኪዳድ ጋቻ እስከ ታኅሣሥ 1997 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ የፍርድ ሒደቱ አልጀመረም።

አዲስ አበባ፣ አምቦ፣ ዓለማያ፣ ናዝሬት፣ አዋሳ፣ ዲላ፣ ደብረዘይት፣ ጂማ እና ባሕር ዳር የሚገኙ ተቋሞችን ጨምሮ በት/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች በጥር 1996 መጀመሪያ አካባቢ በፖሊስና በኦሮሞ ተማሪዎች መካከል ግጭቶች ነበሩ (ክፍል 1 ሐን እና 1መን ይመልከቱ)። ተቃውሞዎች ካተኮሩባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መንግሥት የኦሮሞን መዲና ከአዲስ አበባ ወደ ናዝሬት (አዳማ) ማዛወሩን ባለመቀበል ነበር። በብዙ ት/ቤቶች የኦሮሞ ተማሪዎችን ተቃውሞ እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 330 የኦሮሞ ተማሪዎች መባረርን ተከትሎ (ክፍል 2 ለን ይመልከቱ) ሞትና መቁሰልን ያስከተሉ በርካታ ግጭቶች ነበሩ። አምቦ ላይ ት/ቤት ውስጥ በፈነዳ ቦምብ በርካታ ተማሪዎች ሞተዋል፣ ሌሎችም ቆስለዋል። አዳማ ግብርና ኮሌጅ እና አዳማ የቴክኒክ ኮሌጅ ጩቤዎችና ዱላዎች በያዙ የኦሮሞና የትግሬ ተማሪዎች መካከል በተደረገ ረብሻ የተወሰኑ ተማሪዎች በጠና ቆስለዋል። አንዳንድ ዘገባዎች እንደገለጹት ከዩኒቨርሲቲዎች የተባረሩ የተወሰኑ የኦሮሞ ተማሪዎች ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው እንደተመለሱ ታስረዋል። በሚያዝያ ወር 1996 ዓ.ም. 600 ያህል የኦሮሞ ተማሪዎች በኬንያ ጠረፍ በኩል ተሰድደዋል። ምንም እንኳን ስጋቱ ባይበርድም በዓመቱ የመጨረሻ አጋማሽ ላይ ሁከቱ ቀዝቅዟል። በዓመቱ መጨረሻ በአብዛኛው ሁሉም ተማሪዎች ስለመመለሳቸው ተዘግቧል።

በዓመቱ ውስጥ በጉሳዎች መካከል በተደረጉ ግጭቶች በተለይም ከፍተኛ ትኩረት ያገኘውንና ከታኅሣሥ 1995 እስከ ግንቦት 1996 የቀጠለውን የጋምቤላ ረብሻ ለማቆም የጸጥታ ኃይሎች ተሳትፈዋል። በታኅሣሥ 1995 ያልታወቁ ሰዎች ጋምቤላ ክልል ውስጥ ኢታንግ በተባለው ቀበሌ አካባቢ አንድ ተሽከርካሪን በደፈጣ በማፈን

የጋምቤላ ክልል ተወላጆች ያልሆኑ 8 የመንግሥት ሹማምንት ገደሉ። ይህንን የፈጸሙት አኝዋኮች ናቸው በሚል ጥርጣሬ፣ ለሶስት ተከታታይ ቀናት፣ ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት ባሉበት፣ በተካሄደ የብቀላ ሁከት ከ100 በላይ አኙዋኮች ተገደሉ። የፌዴራሉ ፓርላማም ሁኔታውን የሚያጣራ ኮሚሽን በመሰየም የግድያውን ሁኔታና ምናልባትም በግድያው የወታደሩ እጅ መኖር አለመኖር እንዲጣራ አዘዘ። ኮሚሽኑም 65 ሰዎች መገደላቸውን፣ ከእነዚህ ውስጥም 13ቱ በሠራዊቱ አባላት መገደላቸውን አረጋገጠ። ከጋምቤላ ክልል ከተመረጠ የፌዴራሉ ፓርላማ አባልና የሌሎች ወገኖች ዘገባዎች ግን በመከላከያ ሠራዊት አባላት የተገደሉት ሰዎች ብዛት ከኮሚሽኑ አሀዝ በላይ መሆኑን ገልጸዋል። በአንድ ወገን የታጠቁ አኝዋኮች፣ በሌላ ወገን ደግሞ የመንግሥት ኃይሎችና ጋምቤላ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ከሌሎቹ የአገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች የመጡ ደገኞች የተሳተፉበት ብጥብጥ በዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ቀጥሏል። የተወሰኑት ሁከቶች አደገኞች ነበሩ። በጥር መጨረሻ 1996 አካባቢ፣ በወታደሮችና በአኝዋኮች መካከል ፉኝዶ አጠገብ በተካሄደው ውጊያ፣ ሰላማዊ ሰዎችን ጨምሮ፣ 50 ሰዎች መሞታቸው የተዘገበ ሲሆን፣ ጥር 29 እና 30 1996 ደግሞ ዲማ አጠገብ በተነሳ ግጭት 196 ሰዎች ተገድለዋል። ከጋምቤላ ከተማ ውጭ ያሉ በርካታ ክሊኒኮችና ት/ቤቶች ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል፣ ገበሬዎችም ማረሳቸውን አቋርጠዋል።

በሶማሌ ክልል፣ ዋርደር ዞን ሰኔ 9 እና 10፣ በኦጋዴንና በመጀርቲ ጐሳዎች መካከል በተቀሰቀሰው ግጭት 54 ሰዎች ሞተዋል።

እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ በቀደሙት ዓመታት የተከሰቱ የጐሳ ግጭቶችን በሚመለከት በመንግሥት ዕልባት ያገኙ ጉዳዮች አልታዩም። የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኮንግሬስ በዘገባው መሠረት፣ ቴፒ ላይ በ1995 ከተነሳው ብጥብጥ ጋር በተያያዘ ታግተው ከነበሩት 127 ተጠርጣሪዎች መካከል 12ቱ በጥቅምት ከእገታ ተለቀዋል። ሌሎቹ ደግሞ ብጥብጥ እንዲፈጠር በማነሳሳታቸው ክስ የተመሠረተባቸው ቢሆንም እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ፍርድ አላገኙም።

በቀደሙት ዓመታት ከነበረው በሚለይ ሁኔታ፣ በስደተኞችና በነዋሪዎች መካከል የጐሣ ግጭቶች ስለመኖራቸው ምንም ዘገባዎች አልነበሩም።

በቀደሙት ዓመታት ከነበረው በሚለይ ሁኔታ፣ ኤርትራውያን ስለመገለላቸው በዓመቱ ውስጥ ዘገባዎች አልነበሩም።

## ሌሎች ማህበራዊ ጥቃቶችና እና ማግለል

በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ግብረ ሰዶም የተከለከለና ቀላል የእሥራት ቅጣት የሚያስከትል ሲሆን፣ የከፋ ሁኔታ ሲያጋጥም ቅጣቱ ከ3 ወራት ያላነሰና ከ5 ዓመት የማይበልጥ ነው። ዕድሜአቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ጥቃት ሲደርስባቸው ግን ቅጣቱ ከ5 እስከ 25 ዓመታት ድረስ ይሆናል። ግብረ ሰዶም በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም፤ በግበረ ሰዶማውያን ላይ የደረሰ አንዳችም ጥቃት አልተዘገበም።

ከኤች አይ ቪ ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች አሁንም በሕብረተሰቡ ይገለላሉ።

## ክፍል 6 የሠራተኛ መብቶች

### ሀ/ በማኅበር የመደራጀት መብት

ሕገ መንግሥቱ ለአብዛኛዎቹ ሠራተኞች የመደራጀትና ማኅበር የማቋቋም መብት ቢሰጥም፣ በተለይ ዳኞች፣ ዓቃቢያነ ሕግና የፀጥታ ሠራተኞችን የሚያካትቱ የመንግሥት ሠራተኞችና መምህራን መደራጀት እንደማይችሉ በሕግ ገደብ ተጥሎባቸዋል። በዓመቱ ውስጥ የመንግሥት በማኅበራት ጉዳይ ጣልቃ መግባት አጋጥሟል።

የሠራተኛ ማኅበር ለማቋቋም ዝቅተኛው የሠራተኛ ቁጥር 20 ነበር። ሁሉም ማኅበራት መመዝገብ የሚገባቸው ቢሆንም፣ መንግሥት የማኅበር ምዝገባውን የመሠረዝ ሥልጣን ነበረው። መንግሥት ይህንን ሥልጣኑን በዓመቱ ውስጥ ለመጠቀሙ ዘገባዎች አልነበሩም። በሕጉ መሠረት አንድ የንግድ ድርጅት ይፋዊ የፖለቲካ ዓላማ ማራመድ አይችልም። የሠራተኛ ማኅበሩ 300,000 ያህል አባላት ነበሩት። ጊዜያዊና የትርፍ ሰዓት የእርሻ ሠራተኞች አልተደራጁም። የእነዚህ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ፣ ጥቅማ ጥቅሞች፣ እና አመቺ የሥራ አካባቢዎች በሚገባ ከተደራጁት ቋሚ የተክል እርሻ ሠራተኞች እጅግ ያነሱ ናቸው።

ነጻው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ) የመንግሥት ማዋከብ ዒላማ ነበር። መንግሥት ለኢመማ ሕጋዊ እውቅና የሰጠ ቢሆንም፣ የመንግሥት ት/ቤቶች አስተማሪዎች በሙሉ በመንግሥት የተፈጠረውና የሚደጐመው ማኅበር (ስሙ ያው ኢመማ) አባላት እንዲሆኑና በግዴታ በወር $0.23 (ብር 2) ከደመወዛቸው እየተቀነሰ ለማኅበሩ መዋጮ እንዲያገ ተደርጓል።

በታኅሣሥ 1995 አካባቢ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አስር ዓመት ለፈጀው ክርክር እልባት ሰጥቷል። በመንግሥት የሚደገፈው ኢመማ በነጻው ኢመማ ሕጋዊ መብትና የንብረት ጥያቄ የሌለው መሆኑን እና ሁሉም የነጻው ኢመማ ንብረቶች እንዲመለሱ፣ እንዲሁም ቢሮው እንዲከፈት ውሳኔ ሰጥቷል። አዲሱና በመንግሥት የሚደገፈው ኢመማ ለጠቅላይ ፍ/ቤት በጥር 1996 ይግባኝ ብሏል። የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምር የጠቅላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለሰጠ፣ ምርመራው እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዓመቱን ሙሉ በመንግሥት ሙሉ ቁጥጥር ስር ሆኖ ቆይቷል።

አሠሪዎች በሠራተኛ ማኅበር አባላትና አደራጆች ላይ አድልዎ እንዳይፈጽሙ በሕግ ቢደነገግም፣ በአንዳንድ ማኅበራት ሪፖርት መሠረት የተወሰኑ ለሠራተኛው ጥቅም የቆሙ ተቆርቋሪ የማኅበር መሪዎች ከሥራ ተባረዋል። ለፍ/ቤት በሚቀርቡ ፋይሎች ብዛት የተነሳ የሠራተኛ ፍ/ቤቶች በውዝፍ ጉዳዮች ላይ ስለሚጠመዱ፣ ሕጋዊ ያልሆነ ከሥራ የማባረር ጉዳይ ላይ እልባት ለመስጠት አብዛኛውን ጊዜ
ዓመታት ይፈጃል። ከ4 ወይም 5 ዓመታት ሙግት በኋላም እልባት ያላገኙ እና የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች በመሆናቸው ከሥራ የተባረሩ ሰዎች አቤቱታዎች መኖራቸውን የማኅበር መሪዎች ጠቁመዋል። በሠራተኞች ወይም በማኅበራት ላይ የሚፈጸም አድልዎን በሚመለከት፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓትና የማጣሪያ ዘዴዎች ነበሩ። በሠራተኛ ማኅበራት አባላት ላይ አድልዎ ፈጽመው የተገኙ አሠሪዎች ለማኅበራቸው በመቆማቸው ያባረሯቸውን ሠራተኞች ወደ ሥራቸው እንዲመልሱ ይገደዳሉ።

ለ. የመደራጀትና በሕብረት የመደራደር መብት